# ዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ

## ሪዝቫን 2020

ለዓለም ባሃኢዎች

እጅግ የምትፈቀሩ ወዳጆች፣

1 ሁለት ብቅ እያሉ ያሉ እውነታዎች እነዚህን ቃላቶች ለእናንተ እንድናካፍል ገፋፍተውናል። የመጀመሪያው እውነታ እያንዣበበ ስላለውና አሰቃቂ ስለሆነው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ አደጋዎች በዓለም ዙሪያ እያደገ የመጣው ንቃተ-ህሊና ነው። በብዙ አገሮች ውስጥ እልቂትን ለመታደግ ጀግንነት የተመላቸውና ቆራጥ እርምጃዎች በጋራ ቢወስዱም፣ በቤተሰቦች እና በግለሰቦች ላይ ሃዘን በመፍጠር እንዲሁም መላ ማህበረሰቦችን ቀውስ ውስጥ በመክተት ሁኔታው እነሆ ከባድ ሆኗል። የመከራ እና የሃዘን ማዕበሎች ከቦታ ወደ ቦታ እየተከሰቱ ነው ፤ እናም ይህ በተለያዩ ወቅቶች፣ በተለያዩ መንገዶች የተለያዩ ሀገሮችን ያዳክማል።

2 ሁለተኛውና በየዕለቱ ይበልጥ ገሃድ እየሆነ ያለው እውነታ፣ የባሃኢ ዓለም ሊታወስ ከሚቻል ግዜ ወዲህ አይቶት የማያውቀውን ተግዳሮት የመቋቋም ብቃት እና ያልተደቆሰ ሕያውነቱ ነው። የሰጣችሁት ምላሽ ድንቅ ነው። ከአንድ ወር በፊት በናውሩዝ ክብረ-በዓል ወቅት ወደ እናንተ ስንጽፍ፤ እነኛ ተለምዷዊ የእንቅስቃሴ ዘይቤያቸው የተስተጓጎለባቸው ማህበረሰቦች ያሳዩዋቸው አስደማሚ ባህሪያትን አፅንዖት ለመስጠት ሞክረን ነበር። ወዳጆች ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥብቅ እየሆኑ የመጡ ገደቦችን እንዲያከብሩ በተጣለባቸው ከዚያን ወዲህ ባሉ ሳምንታት ውስጥ በሆነው ሁሉ የአድናቆት ስሜታችን ይበልጥ ጨምሯል። አንዳንድ ማህበረሰቦች በሌሎች የዓለም ክፍሎች ካገኙት ተሞክሮ በመማር፣ ደህንነታቸው አስተማማኝ የሆኑ እና ፈጠራ የተመላቸው በሕዝቦች ውስጥ ያሉትን የህዝብ ጤና ፍላጎቶች ግንዛቤ ማሳደጊያ መንገዶችን አግኝተዋል። ለቫይረሱ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑት እና ከመስፋፋቱ ጋር ተያይዞ ለኢኮኖሚያዊ ችግር ለሚዳረጉት ልዩ ትኩረት

እየተሰጣቸው ነው፤ ይህን አስመልክቶ በባሃኢ የዓለም የዜና አገልግሎት (Bahá'í World News Service) ላይ የሚወጡት ዘገባዎች እየተከናወኑ ካሉቱ ቁጥር ስፍር ከሌላቸው እንቅስቃሴዎች አኳያ እፍኝ አይሞሉም። እነኚህም፥ በጣም ተፈላጊ የሆኑ መንፈሣዊ ባህሪያትን ለመመርመር፣ ለማስተዋወቅ እና ለማሳደግ በሚደረጉ ጥረቶች ይበልጥ እየታገዙ ይገኛሉ። እንደዚህ ያሉ በርካታ ጥረቶች በቤተሰብ ወይም በግል ደረጃ መደረጋቸው እንዳለ ሆኖ፣ ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን ወይም የመገናኛ መሳሪያዎች በሚያስችሉበት ጊዜ ተመሳሳይ ሁኔታዎችን በሚጋሩ ነፍሳት መካከል ልዩ የሆነ የትብብር ስሜት ሆን ተብሎ እየተጠናከረ ይገኛል። ለጋራ እድገት በጣም አስፈላጊ የሆነው የሕብረተሰብ ኑሮ መስተጋብር አይንበረከክም።

3 የብርሃን ሠራዊት የማይታክቱ ፊታውራሪዎች የሆኑት ብሔራዊ መንፈሣዊ ጉባዔዎች እንዴት ማኅበረሰቦቻቸውን በብቃት እንደመሩና ለተፈጠረው ቀውስ የሚሰጠውን ምላሽ ቅርጽ እንዳስያዙ በማየታችን መንፈሣችን ከፍ ከፍ ብሏል። እንደ ሁልጊዜም ሁሉ ፍቅር የተመላበት የአገልግሎት ዓርማን በጀግንነት ካነገቡ አማካሪዎች እና ረዳቶቻቸው ጠንካራ ድጋፍን አግኝተዋል። መንፈሣዊ ጉባዔዎች በየአገሮቻቸው በፍጥነት ተለዋዋጭ ስለሆኑት ሁኔታዎች ወቅታዊ መረጃ ይኖራቸው ዘንድ በሚገባ እየተከታተሉ ሣለም የዕምነቱን ጉዳዮች ለማስተዳደር፤ በተለይም ምርጫን ማካሄድ በሚቻልባቸው ቦታዎች ይህን ለመከወን አስፈላጊውን ዝግጅቶች አድርገዋል። ተቋማት እና ኤጀንሲዎችም በመደበኛ መልዕክት አማካኝነት ጥበብ ያዘሉ ምክሮች፣ የሚያረጋጉ ማጽናኛዎችን እና ቀጣይ ማበረታቻን ሰጥተዋል። በብዙ አጋጣሚዎችም፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ ከሚነሱ የውይይት መድረኮች የሚመነጩ ገንቢ ጭብጦችን መለየት ጀምረዋል። በናውሩዝ መልዕክታችን ውስጥ ይህ የሰው ልጅ ጽናቱን እየተፈታተነ ያለው ፈተና ታላቅ ማስተዋልን እንደሚለግሰው እንደምንጠብቅ የገለጽነው ተስፋ እነሆ ዕውን መሆን ጀምሯል። መሪዎች፣ ታዋቂ ምሁራን እና ተንታኞች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከሕዝባዊ የመወያያ ርዕስነት ርቀው የነበሩ መሠረታዊ ጽንሰ-ሀሳቦችን እና ድፍረት የተመሉ ተስፋዎችን መዳሰስ ጀምረዋል። ነገር ግን እነዚህ በአሁኑ ጊዜ ገና የመጀመሪያ ጭላንጭሎች ቢሆኑም የጋራ የንቃተ-ህሊና ወቅት ይመጣ ዘንድ እድል እንዳለ ማሳያ ናቸው።

4 የባሃኢ ዓለም አይበገሬነት በተግባር ሲገለጥ ከማየት የሚሰማን እፎይታ፣ ወረርሽኙ በሰው ልጆች ላይ በሚያስከትለው መዘዝ በሚሰማን ሃዘን ለዝቧል። በቃ እንግዲህ፣ ምእመናን እና አጋሮቻቸውም የዚህ ሥቃይ

ተካፋይ እንደሆኑ እናውቃለን። አሁን በዓለም ላይ ያሉ ብዙ ሰዎች ህዝባዊ የደህንነት መስፈርቶችን ከማክበር አኳያ የሚተገብሩት ከወዳጆች እና አዝማዶች ጋር የመራራቅ ሁኔታ፣ ለአንዳንዶች እስከወዲያኛው ላለመገናኘትም መንገዶችን ይከፍታል። በእያንዳንዱ ንጋት ላይ፣ ፀሐይ ከመጥለቋ አስቀድሞ ተጨማሪ ሥቃዮችን መቋቋም ግድ የሚል ይመስላል። በዘለአለማዊ ግዛቶች ውስጥ እንደገና የመገናኘት ተስፋ የሚወዷቸውን በሞት ለሚያጡ መፅናኛ ይሁንላቸው። እነኛ ትምህርታቸው፣ ኑሮአቸው፣ ቤታቸው ብሎም መተዳደሪያቸው ራሱ እንኳ ለአደጋ የሚጋለጥባቸው ልባቸው እፎይታ እንዲያገኝ እና የእግዚአብሔር ጸጋ እንዲከባቸው እንጸልያለን። ስለእናንተ እና ስለምትወዷቸው እንዲሁም ስለወገኖቻችሁ ሁሉ ባሃኦላህን እንማጸናለን እንዲሁም በረከቱና ሞገሱን እንለምናለን።

5 ከፊት የሚጠብቀን መንገድ የቱንም ያህል ረዥም እና አድካሚ ቢሆን፣ ጉዞውን ለመጨረስ ባላችሁ ጽናትና ቁርጠኝነት እጅግ ሙሉ እምነት አለን። የሌሎችን ፍላጎት ከራሳችሁ በማስቀደም፣ ያጡትን መንፈሣዊ ምግብ እንዲመገቡ ለማስቻል፣ እነዛ መልስ ለማግኘት ጥማታቸው የሚበረታውን እርካታ እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲሁም እነዛ ዓለም ትሻሻል ዘንድ ለመሥራት የናፈቁት አስፈላጊው እንዲመቻችላቸው ለማድረግ ከተስፋ፣ እምነት፣ እና የልዕልና ማከማቻዎች ትወስዳላችሁ። እንዴት ለተባረከው ፍጹምነት ከተሠጡ ታማኝ ተከታዮች ከዚህ ያነሰ ልንጠብቅ እንችላለን?

ዓለም አቀፍ ቤተፍትህ

# ዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ
## 9 ሜይ 2020

ለሁሉም ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔዎች

በእጅጉ የምትፈቀሩ ወዳጆች፣

1 የአምስቱ ዓመት ዕቅድ የመጨረሻው ዓመት ከነዚያ ከቀደሙት አራት ዓመታት የተለዩ ተግዳሮቶችን ማምጣቱ አሁን በጣም ግልጽ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ዓለም፣ የብዙ ሺዎችን ህይወት በቀጠፈ እና የሰው ዘርን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሰፊ ክፍል በጽኑ ባናጋ፣ በፍጥነት እየተስፋፋ ባለ ቫይረስ መዳፍ ውስጥ ተይዛለች። ሆኖም የባሃኢ ማህበረሰብ እርጋታውን እንደጠበቀ ከፊቱ ለተደቀኑት አጣዳፊ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ሰጥቷል። ለህብረተሰቡ መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎቶች በሰፊው ምላሽ የመስጠት ሚናውን እየተወጣ፣ የማህበረሰብ ህይወት ቀጣይነትን የማረጋገጫ መንገዶች አግኝቷል፤ በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ተገቢ የሆነ ምላሽ። እስካሁን የተከናወኑትን ተግባሮች ሁሉ እናደንቃለን። ሆኖም፣ አሁን፣ መጪው ዓመት ይዞት ሊመጣ የሚችለውን በይበልጥ በምልአት መፈተሽ እንፈልጋለን። በዕቅዱ የመጨረሻ ወራት ግስጋሴውን ለማነቃቃት የምታደርጉት ጥረት፣ ወዳጆች እየተገለጠ ላለው ሉላዊ ቀውስ የሚሰጡትን ምላሽ የመምራት አጣዳፊ ኃላፊነታችሁን በምትወጡበት መልኩ መቀረፁ አይቀሬ ነው። እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች በቀጥታ እንድንጽፍላችሁ ግድ ይላሉ፤ ይህንን መልዕክት በሙሉም ሆነ በከፊል፣ ተገቢ ነው ብላችሁ ባሰባችሁት መልክ ለማህበረሰቦቻችሁ ማካፈል ትችላላችሁ።

2 በአምስት ዓመቱ ዕቅድ መጨረሻ አምስት ሺህ መጠነ ሰፊ የእድገት መርሃግብሮች የማየት ፍላጎታችንን ስንገልጽ፣ የሚያስከትለውን የሥራ ጫና ጠንቅቀን እናውቀው ነበር፤ ነገር ግን የዓለም ሁኔታ እሱን ነበር የሚጠይቀው። በሁሉም ቦታ የእድገት መርሃግብሩን የማጠናከር ሥራ እንዲቀላጠፍ ጥሪ አቀረብን። የእምነቱ ደጋፊዎች፣ ከዚህ በፊት ያልታየ ጥረት በማድረግ እንዴት ወደ እንቅስቃሴ እንደገቡ ማየታችን አስደስቶናል።

በአራት ዓመት ጊዜ ውስጥ የባሃኢ ማህበረሰብ በዓለም ዙሪያ የሚካሄዱ ዓበይት እንቅስቃሴዎችንም ሆነ ተሳታፊዎቻቸውን በእጥፍ አሳድጓል። እንደዚህ ባለ አጭር ጊዜ ውስጥ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ግለሰቦችን በማህበረሰቡ እንቅስቃሴዎች እቅፍ ውስጥ ማምጣት፣ በተከታታይነት በተተገበሩት ዕቅዶች ውስጥ በነበሩት የቀደሙት ዕቅዶች አቻ የሌለው የአቅም እመርታ ነው።

3 እናም ብዙ ተከናውኗል፤ ይህም የባሃኢ ማህበረሰብን ጥንካሬና በራስ መተማመንን ግልጽ አመላካች ነው። ነገር ግን፣ አሁን እንደምትረዱት ያለንበት ቀውስ ዕቅዱን የምናስፈፅምበትን አውድ ለውጦታል። ከዚህ ከአዲሱ እውነታ ጋር እራሳቸውን ለማስማማት ትልቅ እርምጃዎች በወሰዱት ማህበረሰቦች ቁጥር ተገርመናል። ይህን ወቅት በትዕግስት እንደሚታለፍ መስተጓጎል ከማየት ይልቅ፣ የዓለም ሁኔታ ለሰው ዘር ትርጉም ያለው ግልጋሎት የመስጠትን ኃላፊነት አንገብጋቢ እንዳደረገው ተገንዝበዋል። እንደሚጠበቀው፣ የሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ከሚታዩት ሁኔታዎች ጋር መስማማት አለባቸው፣ ነገር ግን ጊዜው የተከበሩ አላማዎች፣ የከፍተኛ ቁርጠኝነትና የከባድ ጥረት እንደሆነ ምንም ጥርጥር ሊኖር አይገባም። በሚገባ እንደሚታወቀው፣ የዕቅዱ እንቅስቃሴዎች፣ በሂደት ለግዙፍ ተግዳሮቶች ጽናትን በማጎልበት፣ እጅግ ስኬታማ የሆነ የማህበረሰብ መንፈስን ለማሳደግ ያለሙ ናቸው። የማስተማር ጥረቶች ለማህበረሰቡ መንፈሳዊና ቁሳዊ ደህንነት ድርሻቸውን የሚያበረክቱ ቁጥራቸው እያደገ የሚሄድ ነፍሳትን ማፍራት ላይ ያነጣጥራሉ፤ የአምልኮ ስብሰባዎቹ የአገልግሎት መንፈስን በጋራ የአምልኮ ስብሰባ ውስጥ ስር ሰዶ እንዲያብብ በማድረግ ይንከባከቡታል። በአጭሩ፣ ዕቅዱን ማራመድ ማለት በሰው ዘር ህይወት ውስጥ የመራራ ስቃይ ጊዜ የሆነውን የአሁኑን ዓይነት ጊዜ ጨምሮ በማንኛውም ጊዜና ወቅት የአገልግሎት ጎዳናን ለመጓዝ አቅም መገንባትን ያመለክታል። እንግዲህ በዓለም የአሁኑ ሁኔታ ላይ እንዴት የዕቅዱ የተግባር ማዕቀፍ ሥራ ላይ እንደሚውል ለመማር መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች በትጋት መቀጠላቸው አስፈላጊ ነው፤ ይብዛም ይነስም ሉላዊው የጤና ቀውስ በባሃኢ እንቅስቃሴዎች ላይ ለወራት ምናልባትም ለዓመታት ቀጥተኛ ተፅዕኖ ማሳረፉ አይቀሬ ይመስላል፤ ስለሆነም ከዚህ ሁኔታ ጋር የመለማመዱ ሥራ ጊዜ የሚሰጠው አይደለም። በዚህ ረገድ በዓለም አቀፍ የትምህርት ማዕከል በሚገባ የሚመሩት አህጉራዊ አማካሪዎችና ረዳቶቻቸው፣ ወዳጆችን የማነቃቃትና የተሰጣቸውን ሥራ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው አቅጣጫ

በማሳየት ጥረታቸው አስገራሚ ቁርጠኝነት አሳይተዋል፤ በሚቀጥሉት አራት ዑደቶችና ከዚያም በኋላ እንዲሁ እንደሚቀጥሉ አያጠራጥርም።

4 በእርግጥ፣ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ለጊዜው መቆምና አሁን ላለው ሁኔታ ተስማሚ ያልሆኑ ስልቶችና አሰራሮች ለጊዜው ገታ መደረግ እንዳለባቸው እንረዳለን። ነገር ግን፣ የተወሰኑ የእንቅስቃሴ ዕድሎች ለጊዜው ቢዘጉም፣ ሌሎች ተከፍተዋል፤ እናም ያሉትን የእንቅስቃሴ ዘይቤዎች የሚያጠናክሩ አዳዲስ መንገዶች ብቅ ብለዋል። በተቀዳሚነት አካባቢን መሰረት ያደረገው የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ባህሪ አለመበረዙን እንደመከታተል ሁሉ ተጣጣፊነትም እሴትነቱ ተመስክሯል፤ በስብስብ ውስጥ ባሉ ሰፈሮችና መንደሮች ውስጥ በማደግ ላይ ያሉ ማህበረሰቦችን ኮትኩቶ ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶች መቀጠል አለባቸው። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ የአሁኖቹ ሁኔታዎች፣ ደህንነትን ታሳቢ አድርገው በተዘጋጁ ጸሎተ ሱታፌዎችና ጥናት ክበቦች የማህበረሰቡን ተሳትፎ የሚያሰፉ ያልተጠበቁ ዕድሎችን ፈጥረዋል። ቤተሰቦቻቸው በቤት አካባቢ እንዲወሰኑ የተደረጉባቸው ብዙ ወላጆች፣ በልጆቻቸው መንፈሳዊ ትምህርት ውስጥ ከተመልካችነት ወደ ዋና ተዋናይነት እንዲሸጋገሩ የተደረገላቸው ድጋፍ አስደስቷቸዋል። የታዳጊ ወጣቶችና የወጣቶች ቡድኖች፣ በጥበብ የሚካሄድ ርህራሄ የተመላው ቀላል የአገልግሎት ተግባርን ኃይል አውቀዋል። ሆኖም፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የአገር አቅኚዎች፣ ተንቀሳቃሽ አስጠኚዎችና ጎብኚ አስተማሪዎችን እንቅስቃሴ የሚፈልጉ እቅዶች እንዲተላለፉ መወሰናችሁ የሚጠበቅ ነው፤ ይሄም ሊያሳስባችሁ አይገባም፣ ሁኔታውን በመጪዎቹ ወራት እንደገና ልታዩት ትችላላችሁ። የሚቀጥለው አንድ ዓመት በአሁኑ ዕቅድ መጨረሻ ሊደረስባቸው የማይቻሉ ማናቸውንም ግቦች ወይም ዓላማዎች ለማሳካት ዕድል ይሰጣል።

5 በዚህ ቀውስ ውስጥ መስራት መቀጠል፣ በብዙ ሁኔታዎች፣ የመዋዕለ ንዋይ እጥረት ውጥረት ውስጥ እንደሚከታችሁ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ብዙዎች እየተጋፈጡት ያለው ኢኮኖሚያዊ ጫና የእናንተን የአቅም ምንጭ ሊገድብ እንደሚችል እንገነዘባለን። ልንረዳችሁ ዝግጁ እንደሆንን እርግጠኞች ሁኑ። ይህን በተመለከተ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ ወይም መደናገር አይኑር፡- የእምነቱ ተቋማት በዚህ ወቅት በሙሉ *ሥራዎቻቸውን* መቀጠላቸውና አበይት *ሥራዎቻቸውን* ከመስራትም የመዋዕለ ንዋይ እጥረት እንቅፋት አለመሆኑ ወሳኝ ነገር ነው። ያለምንም ጥርጥር በእያንዳንዱ አገር የሚገኙ አማኞች ሁሉ በዙሪያችሁ ይሰለፋሉ፣

በተለይ አቅሙ ያላቸው ወዳጆች እናንተን ለመርዳት ፈቃደኛ እንደሚሆኑ እንተማመናለን።

6 እንደምታውቁት፣ የተለያዩ ህብረተሰቦች ከቀውሱ የሚመነጩ ችግሮችን በሚመክቱባቸው መንገዶች መካከል ከፍተኛ መለያየት አለ፣ ስለሆነም፣ የተለያዩ ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔዎችን የሚገጥሟቸው ተግዳሮቶች የተለያዩ ናቸው። እነዚህም ተግዳሮቶች በጊዜ ሂደት ይቀየራሉ። ይሄም፣ የአካባቢ፣ የክልልና ብሔራዊ ተቋማት እውነታቸውን ለማንበብ ሲሹና ለአዳዲስ ክስተቶች ንቁ ሆነው ለመገኘት እንዲችሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ቅልጥፍናን ይጠይቃል። እናንተ ከአማካሪዎች ጋር የምታደርጉት ትብብር በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ልናሰርጽባችሁ እንሻለን፡- ለማህበረሰባችሁ ፍላጎቶች በፍጥነት ምላሽ መስጠታችሁን ለማረጋገጥ፣ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ቀድሞ ለመገመት፣ የሚከፈቱ ዕድሎችን ለመጠቀም፣ ተስፋ ሰጪ ተነሳሽነቶችን ለመደገፍ፣ የምትገዙለትና ቀጣይነት ያለው፣ በማያቋርጥ ሁኔታ ተከታታይነት ያለው የመረጃና የግንዛቤ ልውውጥ መሆን አለበት። በትክክል ምን ዓይነት እርምጃዎች በባሃኢ ተቋማት መወሰድ አለባቸው የሚለው በእርግጥ በተከሰቱት ሁኔታዎች ይወሰናል። ነገር ግን በእያንዳንዱ አካባቢ ወዳጆች ግልጽና ጊዜውን የጠበቀ መመሪያ ይፈልጋሉ፤ ለእነዚያ በራሱ በቫይረሱ ወይም በመስፋፋቱ ምክንያት በሚያደርሰው የኢኮኖሚ ተጽዕኖ አደጋ ላይ ለወደቁት የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፤ እንዲሁም በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ የማህበረሰቡን የጋራ መንፈስ ለማስቀጠል ፈጠራ የተመሉ አቀራረቦች ያስፈልጋሉ። ቤተሰቦችን፣ ተጎራባች ቤተሰቦችን፣ ወይም ሌሎች ቡድኖችን ያካተቱ የተለያዩ የትስስር መረቦች ለሌሎች ጠቃሚ ድጋፎች እያደረጉ ነው፤ በማህበረሰባችሁ ዘዴኝነት መተማመንና ችሎታዎቻቸውንና ኃይሎቻቸውን አሟጣችሁ ለመጠቀም መሞከር አለባችሁ። አሁን በአንዳንድ ቦታዎች ሁኔታዎች በጣም ቢከብዱም፣ እስካሁን ወረርሽኙ ከሚያስከትለው ከበድ ካሉ ጉዳቶች የተረፉ አገሮች ውስጥ ያሉ ብሔራዊ ጉባዔዎች የባሰ ሊመጣ እንደሚችል ማሰብ አለባቸው፤ እናም ለዚህ አይቀሬ ሁኔታ ከአሁኑ የሚደረግ ማንኛውም ዝግጅት ይህን መሰል ጥረቶችን ሊገቱ የሚችሉ ገደቦች ከመጣላቸው በፊት፣ ከአሁኑ ባለመረበሽ ግን ሳይዘገይ መጀመር አለባቸው። በተለይ የአካባቢ መንፈሳዊ ጉባዔዎች እነሱ የማይነጠል አካል በሆኑበት በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ ይህንን ለመከላከል፣ ለማዳን ወይም ችግሩን ለማቅለል በእነርሱ አቅም ምን መንገድ መከተል እንደሚችሉ ማየት አለባቸው።

7 ማህበረሰቡ በእንደዚህ ዓይነት ችግርና ሥቃይ ውስጥ ሲሆን፣ የባሃኢዎች በሰው ዘር ጉዳዮች ላይ ገንቢ አስተዋጽኦ የማድረግ ሃላፊነታቸው ይበልጥ ይጎላል። አሁን ጊዜው ራሳቸውን የቻሉ ሆኖም ግን የተያያዙ የተግባር መስመሮች ወደ አንድ ነጥብ የሚመጡበት ነው፣ ለአገልግሎት ጥሪ የሚስተጋባበት። ስልጣኔን በማራመድ የማይነጣጠሉ ተዋናዮች የሆኑት ግለሰቡ፣ ማህበረሰቡና የእምነቱ ተቋማት ኃላፊነታቸውን በመወጣትና እርስ በእርስ ባላቸው ግንኙነት በሚገለጸው ያደገ ብስለት የሚታወቀውን ለየት ያለውን የባሃኢ የህይወት ዘይቤ የሚያሳዩበት ደረጃ ላይ ናቸው። የእምነቱን ሕብረተሰብ የመገንባት ኃይል በምልዓት እንዲያሳዩ ተጠርተዋል። ለማህበራዊ አገልግሎት የተመሰረቱ ኤጀንሲዎችና ፕሮጀክቶች አቀራረባቸውን እየሰፋ የሚሄደውን ፍላጎት በሚያረካ መልኩ ማስተካከል ይኖርባቸው ይሆናል፤ ይህን ለመፈፀም የሚደረጉ ጥረቶች እየተካሄዱ ያሉ መርሃግብሮችን ይበልጥ ጥልቅ በሆነ ትርጉምና ዓላማ እንዲሞሉ ያደርጓቸዋል። ከዚህም አልፎ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ እየተካሄዱ ባሉ አዳዲስ ውይይቶች የባሃኢዎች አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ጉጉትን እየቀሰቀሰ ነው፤ እዚህም መወጣት ያለብን ኃላፊነት አለ። በሰው ዘር አንድነት የማያሻማ እውነት ላይ የተመሰረተ ከፍ ያለ የውህደት ደረጃን መቀዳጀት አንገብጋቢነት ቁጥራቸው እየጨመረ ለሚሄድ ሰዎች ግልጽ እየሆነ በመጣበት በዚህ ጊዜ፣ ህብረተሰቡ የእንዲህ አይነቱ የላቀ ግብ መሰረቶች የሆኑትን መንፈሳዊ መርሆዎች በጠራ መልኩ ማብራራት የሚችሉ ግልፅ ድምፆች ያስፈልጉታል።

8 በእርግጥ ኃላፊነታችሁ የማህበረሰቡን ጉዳዮች ከማስተዳደርና ኃይሎቹን ወደተከበሩ ግቦቹ ከመምራት ያለፈ እንደሆነ ሁሌም ትገነዘባላችሁ፡- ለእያንዳንዱ እርግጠኛ አማኝ ሁሌም ዝግጁ ሆነው ስለሚጠብቁትና ባስፈለገ ጊዜ ለክተት ጥሪ መሰለፍ ስላለባቸው መንፈሳዊ ኃይሎች ግንዛቤውን ለማሳደግ ትሞክራላችሁ። እነዚህ ኃይሎች ናቸው ማህበረሰቡን ችግርን የመቋቋም አቅም የሚቸሩት፣ ፅኑነቱን የሚያረጋግጡት፣ የሰውን ዘር የማገልገልና የወደፊት እይታውን ከፍ የማድረግ መለኮታዊ ተልእኮው ላይ እንዲያተኩር የሚያደርጉት።

9 ይሄ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ሃገሮች ወደ አንድነት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መጠን ለመገመት አይቻልም። ነገር ግን የባሃኢ ማህበረሰብ ለሚከውናቸው ሥራዎች፣ ከፊታችን ያሉት ወራት ወሳኝ ለመሆናቸው ምንም ዓይነት ጥርጥር የለም። በእርግጥም ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም። ይህ የመጨረሻው ዕቅድ፣ የመጨረሻው ዓመት፣

በተከታታይ የግንባታው ዘመን የመከፈቻ ምዕተዓመት የመጨረሻውን ሩብ ምዕተዓመት ያጠቃለለ፣ የሚቀጥሉት ተከታታይ ሉላዊ ሥራዎች የሚያርፉበትን መሠረት ይደመድማል። ይህ መጨረሻው እስካሁንም ያልተፃፈ፣ ማራኪ የሆነ ድራማ፣ የመጨረሻው ትዕይንት ነው።

10 ከሃሳባችን ርቃችሁ አንዲት ቅፅበት እንኳን አታልፍም። ይህንን ተግዳሮት ለመጋፈጥ ባላችሁ አቅም ላይ ያለን ሁሉም እምነትና ልበሙሉነት የሚመነጨው የመጨረሻ ደጋፊያችሁና ረዳታችሁ የአብሃ ውበት ራሱ መሆኑ ካለን እውቀት ነው። በቅዱሱ ደጀሰላም ላይ በምናደርገው ተማጽኖ፣ የእርሱ ጸጋ ለሰው ዘር የሚፈስባቸው ንጹህ ማስተላለፊያዎች እንዲያደርጋችሁ እንለምናለን።

ዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ